በራይንሐርድ ቦንኬ

# የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት

## ምንድነው? እንዴትስ ማግኘት ይቻላል?

# The Holy Spirit Baptism

1,471,000 copies printed

1st Amharic Edition 1994

ISBN 3-9803469-4-3

© Christ for all Nations

Cover Artwork By K. Schablowski

Typeset by Logos Ethiopia

Translated by Tesfaye Mesfin

ትርጉም - በተስፋዬ መስፍን

Printed in Egypt



## የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ምንድነው?

### ዐዋጅ ነጋሪው።

በኢየሩሳሌም በነበረው ቤተ መቅደስ ውስጥ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ተሰብስበዋል፤ ከዚያ በፊት ሰምተውት የማያውቁትን ግሩምና ውብ ለዛ ያለውን ቃል ሊሰሙ ነው። ወቅቱ ብሔራዊው በዓል ከመፈጸሙ በፊት የመጨረሻው አምልኮ ሥነ-ሥርዓት የሚከናወንበት ዕለት ነበር። የሁሉም ዓይን ውኃና ወይን ጠጅ የተሞላውን የወርቅ ማድጋ (እንስራ) በአትኩሮት ይመለከታሉ። ለእግዚአብሔር የመጠጥ መስዋዕት ሊያቀርቡ ነው። ካህኑ በሁሉም ፊት አንጸባራቂውን የወርቅ ማድጋ ወደ ፀሐይ አነሳው፤ ወዲያውኑም በተመስጦ ተዋጠ። ውኃው በነሐስ መሰዊያ ላይ ሲረጭ የሚሰጠውን ድምፅ ለመስማት ሕዝቡ ሁሉ በታላቅ ጸጥታ ይጠብቃሉ።

ወዲያውኑ አንድ ድምፅ ጸጥታውን አቋረጠ። ከሺህ ዓመታት ወዲህ ተሰምቶ የማያውቅ ድምፅ። ብርክ የሚያስይዝ ድምፅ። ድምፁ የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ድምፅ ነበር። ገና ከመጀመሪያውኑ ሰማይና ምድርን ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣ ድምፅ ነው። በዚያ ቤተ መቅደስ በሕዝቡ ፊት ቆመና-

> «ውኃ የጠማው ቢኖር ወደ እኔ መጥቶ ይጠጣ፤ በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንደሚለው፤ የሕይወት ውኃ ምንጭ ከውስጡ ይፈልቃል።» (ዮሐ. 7፥37-38) በማለት ዐወጀ።

ትኩስ፥ ንጹሕ፥ ጥዑም፥ እጅግ ብዙ እና የማያቋርጥ «የሕይወት ውኃ ምንጭ» እንጂ፥ በሰው ሰራሽ ዕቃ የሚወሰን ውኃ አይደለም።

አንዳንድ ሰዎች እንደ ጠርሙስ ወይም እንስራን በመሳሰሉ አነስተኛ የውኃ መያዣዎች ተወስነውና ረክተው ይኖራሉ። በዓለማችን ብዙ ታላላቅ የገበያ አዳራሾች (ሱፐር ማርኬት) አሉ፤ ትኩስ ትኩሱን ለተጠቃሚው ማቅረብ ግን አልቻሉም። አንዳንድ ጊዜ የነፈሰበትን፥ የታሸገውን፥ የጠወለገውንና ለዛ ያጣውን ነው የሚያቀርቡልን። እንዴት እንደምንኖር ሊያሳዩን፥ ኖረዋል ተብለው የሚገመቱትን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ምሳሌነት ይቀርቡልናል።

> ኢየሱስ ግን አሁን የምንኖረውን ሕይወት ሊሰጠን መጥቶአል። ማንም እንሁን፥ ምንም እንሁን ሕይወትን አሁን የሚኖር ሕይወት አድርጎታል።

ሰዎች ሁሉ «የመኖር» ናፍቆት አላቸው። ይሁን እንጂ መኖር የሚቻል የሚመስላቸው ግን :- ሁኔታዎች እነርሱ እንደሚፈልጉዋቸው ሲሆኑላቸው፥ ብዙ ገንዘብ ሲያገኙ፥ ትዳር ሲመሠርቱ ወይም ጡረታ ከወጡ በኋላ በቂ የመዝናኛ ጊዜ ሲኖራቸው ብቻ ይመስላቸዋል። ኢየሱስ ግን አሁን የምንኖረውን ሕይወት ሊሰጠን መጥቶአል። ማንም እንሁን፥ ምንም እንሁን ሕይወትን አሁን የሚኖር ሕይወት አድርጎታል። አሁኑኑ ጀምረን መኖር እንጂ፥ የወደፊቱን ሕይወት መጠበቅ የለብንም።

እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ 40 ዓመት ሙሉ በምድረ በዳ መርቶአቸዋል። በነዚያ ዓመታት ይጠጡ የነበረው የረጋ፥ የታቆረና ጣዕሙን ያጣ ውኃ አልነበረም። ትኩስ፥ ንጹሕና ለመጠጥ የሚጣፍጠውን ውኃ ነበር ከዓለት ያመነጨላቸው። (ዘፀ. 17፥1-7) በመቅደሱ ውስጥ የመጠጥ ቁርባን ይቀርብ የነበረውም፥ ለዚያ ከዓለት ለመነጨ ውኃ መታሰቢያ እንዲሆን ነበር። (ዘኍ.



20፥1-13) ኢየሱስ ግን አዲስ ትርጉም ሰጥቶታል፤ ያ፥ የዓለት ውኃ ለመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ምሳሌያዊ ገለፃ ነበር።

## ኢየሱስ ብቻ

ማንም ቢሆን እንደ ኢየሱስ በድፍረት የተናገረና፥ ለእውነተኛው አካል ምሳሌ የሆኑትን የፈጸመ የለም። ፍጥረት ከተከሰተበት ዘመን ጀምሮ የነገሮችን ሁኔታ መለወጥ የሚችል እርሱ ብቻ ነው። በእርሱ አማካይነት አዲስና በሰዎች ተሰምቶ የማያውቅ ነገር ከሰማይ ወደ ምድር ይዘልቃል። ይህንንም :- «አብ የሰጠው ተስፋ» (የሐዋ ሥራ 1፥4) ብሎታል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከ8,000 የሚበልጡ ተስፋዎች ተሰጥተዋል፤ ይህ ተስፋ የተሰጠበት ሁኔታ ግን ከሌሎች የተለየና የላቀውን ስፍራ የያዘ አድርጎታል። አብ የሰጠውንም ስጦታ ለእኛ ሰጥቶናል። ይህንንም አስመልክቶ መጥምቁ ዮሐንስ :-

> «እኔ ራሴ አላውቀውም ነበር፤ ነገር ግን በውኃ እንዳጠምቅ የላከኝ ‹መንፈስ ቅዱስ ሲወርድና ሲያርፍበት የምታየው፥ በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ እርሱ ነው ሲል ነግሮኛል። እኔም ይህን አይቻለሁ፤ ስለዚህ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን እመሰክራለሁ» (ዮሐ.1፥33-34) ብሏል።

## የተለያየ አገላለጽ

ከላይ በቀረበው ጥቅስ እንደምንመለከተው ዮሐንስ «የሕይወት ውኃ ምንጭ» ከሚለው ቃል ይልቅ በተለየ አገላለጽ ዘይቤ ነው የተጠቀመው። ቅዱሳት መጻሕፍት

በተለያየ ሁኔታ ያቀርቡታል። ለምሳሌም ያህል ፡- በእሳት መጠመቅ፥ (ማቴ.3፥11፤ ሉቃ.3፥16) ኃይልን መልበስ፥ (ሉቃ. 24፥49) በእግዚአብሔር ዘይት መቀባት፥ በመንፈስ መስጠም (መጠመቅ)፥ «በመንፈስ መሞላት» (ኤፌ. 5፥18) በመንፈስ መመላለስ፥ በመንፈስ መጸለይ፥ በመንፈስ መኖር፥ (ገላ. 5፥25፤ ሮሜ 8፥26) ይሉታል።

ከዚህም በላይ ሰውነታችን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እንደሆነና፥ (1 ቆሮ. 6፥19) መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ከክርስቶስ የተለየ ሌላው አፅናኝ መሆኑን ያመለክታሉ። (ዮሐ.14፥16)

ከላይ የተመለከትናቸው ቃላት በንድፈ-ሃሳብ ደረጃ የቀረቡ ቢሆኑም የተለያየ መልክና ዝርዝር ታክሎባቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ አሠራር የተለያየ ስዕላዊ ሃሳቦችን ይዞአል። ምልክቶች፥ ድንቆችና ተአምራትም የእርሱ ውጤቶች ናቸው። ከመንፈስ ቅዱስ ሥራ የተነሣ ሐዋርያቱ «ከኢየሱስ ጋር እንደነበሩ» ታውቆአል፤ ከመንፈስ ቅዱስ ሥራ የተነሣ ሐዋርያት ዓለምን «በትምሕርታቸው ገለባብጠዋል»፥ (ኤፌ. 2፥5) ጌታን ማወቅ የሚቻለውና አዲስ የሕይወት ልምምድ ማግኘት የሚቻለውም ከመንፈስ ቅዱስ ነው። ከአጉል ስሜታዊነት፥ ከተለምዶ ቤተክርስቲያን ሳሚነት አልፎ ሕያውና ፍልቅልቅ እምነት የሚኖረን ከመንፈስ ቅዱስ ሥራ የተነሣ ነው። ጳውሎስም ፡- «እንድትድኑ እጅግ ከተከበረው ኃይሉ ብርታትን ማግኘት ትችላላችሁ» (ቆላ. 1፥11) ይላል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱም ፡- «መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ» (የሐዋ. 1፥8) ብሏል።

እኛ ዳግም የተወለድን ክርስቲያኖች የተለየን ነን፤ ቅዱሳን ነን፤ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትም ክርስቶስን እንደግል አዳኝ አድርገን ከመቀበል ቀጥሎ የምናገኘው ከፍተኛ ልምምድ ነው። ይህም የሚቻለው በኢየሱስ ብቻ ነው። ኢየሱስ ለእኛ ሲል ሞቶአል፤ ከሞትም ተነሥቶአል፤



በእግዚአብሔር አብ ቀኝ በክብር ተቀምጦአል። ይህንንም ስጦታ አድሎናል። ዕፁብ ድንቅ ስጦታ!

## መንፈስ ቅዱስ ማነው?

ጌታ ስለማንነቱ ሁሉንም አብራርቶ የሚያስረዳን መልእክተኛ ከሰማይ አልላከልንም። በመንፈሱ አማካይነት የሚሠራውን ሥራ መመልከት ይቻላል። መንፈስ ቅዱስ ሰብዕና (ፐርሰናሊቲ) አለው፤ መንፈስ ቅዱስ ማለት እግዚአብሔር በድርጊት ወይም በእንቅስቃሴ ላይ ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ በውሆች ላይ ከመስፈፉ የተነሣ ፍጥረት ተገኘ። (ዘፍ. 1፥2) እግዚአብሔር በመረጣቸው አገልጋዮችም ላይ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዲያድርባቸው አደረገ።

ኢየሱስ የተናገረውም ስለዚሁ መንፈስ ነው። የጥበብና የዕውቀት መንፈስ፤ የመፍጠር ኃይል ያለው መንፈስ፤ ኃይልና ፈውስን የሚሰጥ የብርታት፥ የመታመንና የቅድስና መንፈስ።

> «እግዚአብሔርም ባስልኤልን መርጦታል ... እግዚአብሔርም እርሱን በመንፈስ ኃይል እንዲሞላ አድርጎ ማናቸውንም የጥበብ ሥራ መሥራት እንዲችል ብልኀነትን፥ ችሎታንና ማስተዋልን ሰጥቶታል።... ለእርሱና ለአሆሊብ የማስተማርን ችሎታ ሰጥቶአቸዋል»። (ዘፀ. 35፥30፤ 31-34)

«የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ላይ ስላደረ (በዖቲንግል) የእስራኤል መሪ ሆነ።» (መሳ. 3፥10)

የእግዚአብሔር መንፈስ በጌዴዎን ላይ ወረደ (መሳ. 6፥34) እርሱም የእስራኤልን ሕዝብ ታደገ። (መሳ.

6፥11-8፥35) መንፈስ ቅዱስ ለሳምሶን ከሰብዓዊ አእምሮ በላይ የሆነ ኃይል ሰጠው። (መሳ. 13፥1-16፥31) የእግዚአብሔር መንፈስ በዮፍታሔ ላይ ወረደ፤ ጠላቶቹንም በእጁ አሳልፎ ሰጠው። (መሳ. 11፥1-12፤ 7)

ከመሳፍንት ዘመን በኋላ ዕድሜውን በሙሉ የእስራኤልን ሕዝብ የመራው ነቢዩ ሳሙኤል ነበር። እንዴት? በመንፈስ ቅዱስ የተመሩ ሰዎች ከእግዚአብሔር ተመርተው የተናገሩት ነው። (2 ጴጥ. 1፥21) ነቢዩ ሚልክያስ ደግሞ በእግዚአብሔር መንፈስ መሞላቱን ተናግሮአል። (ሚል. 3፥8)

እነዚህ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ስዕላዊ ገለፃዎች ናቸው። ኢየሱስ የተናገረውም ስለዚሁ መንፈስ ነው። የጥበብና የዕውቀት መንፈስ፥ የመፍጠር ኃይል ያለው መንፈስ፤ ኃይልና ፈውስን የሚሰጥ፥ የብርታት፥ የመታመንና የቅድስና መንፈስ።

የእግዚአብሔር ኃይል ታላላቅ ሰብዕና፥ ወይም ከፍተኛ ወኔ ላላቸው ብቻ የሚሰጥ የብርታት ክኒን አይደለም፤ ደካማነታቸውንና ታናሽነታቸውን ተገንዝበው የሚፈልጉት ሁሉ ያገኙታል። «ኃይልን ለደካሞች ይሰጣል፤ ጉልበት ለሌላቸውም ብርታትን ይጨምራል።» (ኢሳ. 40፥29)

## አራት ስዕላዊ ገለፃዎች

መንፈስ ቅዱስን አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱስ አራት ስዕላዊ ገለፃዎችን ይሰጣል፤ አራቱንም በጥንቃቄ እንመለከታለን።

አንደኛ ስዕላዊ ገለፃ ፦ ሙሴ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ በሰባዎቹ ሽማግሌዎች ላይ እጁን ጫነባቸው፤ መንፈስ ቅዱስም ወረደባቸው። ልክ በዚያው ጊዜ በሰፈር ቆይተው በነበሩት በኤልዳድና ሜዳድም ላይ መንፈስ



ቅዱስ ስለወረደባቸው ትንቢት ተናገረዋል። ይህንንም የተመለከተው አንድ ወጣት እየሮጠ ወደ ሙሴ ሄደና «ኤልዳድና ሜዳድ በሰፈር ውስጥ ትንቢት እየተናገሩ ነው፤ ጌታዬ ሙሴ ሆይ እባክህን ከልክላቸው አለው» ሙሴ ግን አልከለከላቸውም፤ አልተቃወማቸውም። እንዲያውም ፦ አንተ ስለ እኔ ትቀናለህን? እኔስ እግዚአብሔር በሕዝቡ ሁሉ ላይ መንፈሱን ቢያወርድና እንደነቢያት ትንቢት ቢናገሩ ደስታዬ ነው አለው። (ዘኁ. 11፥29)

በአንድ ጊዜ በሰባ ሰዎች ላይ! ይህም ከ1200 ዓመታት በላይ እንደ ከፍተኛ ቁጥር ሲገመት ቆይቶአል። ይሁን እንጂ፥ ያ ልምምድ አልፎ አልፎ የሚታይ፥ ጊዜያዊና ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ ነበር። ይህ ሙሴ የነበረው ምኞት ግን በዘመናት ሁሉ በብዙዎች ልብ ሲብላላ ኖሮአል።

ሁለተኛው ስዕላዊ ገለፃ ፦ የሰለሞን ቤተ መቅደስ መደበኛ አገልግሎቱን እየሰጠ ቢሆንም፥ ኃጢአት የሕዝቡን ሕይወት በክሎት ነበር፤ ስለዚህም ነቢዩ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ እንደሚፈርድ በኢየሩሳሌም አደባባዮች ላይ ዐወጀ። ነቢዩ ኢዮኤል ዘመናትን አቋርጦ በሕዝቡ ላይ የሚደርሰውን የጦርነት፥ የሽብር፥ የጥፋት ዳመና በትንቢት ቴሌስኮፕ ተመልክቶት ነበር፤ ማንም መረዳት እንደሚችለውም ትንቢቱ ተፈጽሞአል። ይሁን እንጂ ኢዮኤል ከዚህ የሚበልጥ ነገር ነበር ለሕዝቡ የተናገረው፤ ከማዕበሉ ባሻገር ብሩህ ሰማይን ተመክቶአል። ነገሮች የሚሻሻሉበትን ብቻ ሳይሆን ፍጹም አዲስ የሚሆኑበትን ቀን ሲያመለክት «ከዚህም በኋላ እንዲህ ይሆናል፤ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፥ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን ያልማሉ፥ ጐበዞቻችሁም ራዕይ ያያሉ፤ ደግሞም በዚያ ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎች ላይ መንፈሴን አፈሳለሁ። በላይ በሰማይ ድንቆችን አሳያለሁ በታች በምድርም ደምና እሳት የጢስም ጭጋግ» (ኢዮ. 2፥28-30) ብሏል።

በዚያ ዘመን የወንዶችና የሴቶች ባሪያዎች ሥራ የጌቶቻቸውን እጅ ማስታጠብ ወይም እግር ማጠብ ነበር፤ እግዚአብሔር ግን በእነርሱ ላይ እንኳ ሳይቀር መንፈሱን እንደሚያፈስ ነው ተስፋ የሰጠው። ይህም ማለት በማንኛውም ሕዝብ ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ እግዚአብሔር መንፈሱን ያፈስሳል ማለት ነው።

> በማንኛውም ሕዝብ ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ እግዚአብሔር መንፈሱን ያፈስሳል።

ይህ ፍላጐትን የሚያነሳሳና ስሜትን የሚያነቃቃ ተስፋ ነው። ከዚህ ቀደም ለጥቂት ምርጥ አገልጋዮች ብቻ ይታደል የነበረው ስጦታ የእርሱ ለሆኑት ሁሉ የሚሰጥ መብት ሆኖአል። ብዙዎች ይህን መቀበል ያዳግታቸዋል፤ ለብዙዎችም ከሚያስቡት በላይ ይሆንባቸዋል። ይሁን እንጂ፥ እግዚአብሔር ተናግሮታል፤ የእግዚአብሔር ቃል ደግሞ ዝንፍ አይልም።

ሦስተኛው ሥዕላዊ ገለፃ :- መጥምቁ ዮሐንስ የተለመደ የማጥመቅ አገልግሎቱን ለማከናወን በዮርዳኖስ ወንዝ ዳርቻ ቆሞአል። ዮሐንስ ከ400 ዓመታት በኋላ የተነሣ የእግዚአብሔር ነቢይ ነበር። ብዙዎቹ ትምሕርቱን ለመስማትና ለመጠመቅ ወደ እርሱ እየመጡ ነው። ጠንከር ያለው መልእክቱ ሕዝቡን ለንስሐ አዘጋጅቶአቸዋል። ለዘመናት ሲጠበቅ የኖረውም መሢሕ ሊመጣ ነው።

> «እኔስ ለንስሐ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፤ ጫማውን እሸከም ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል።» (ማቴ. 3፥11)

ይህን ከተናገረ ከሃያ አራት ሰዓት በኋላ ኢየሱስ ውኃውን እየሰነጣጠቀ መጥቶ በመጥምቁ ዮሐንስ ፊት ቆመ። ዮሐንስም - «ኢየሱስ ሆይ፥ አንተን ለማጥመቅ ብቁ አይደለሁም፤ እኔ ነኝ በአንተ መጠመቅ የሚገባኝ» በማለት ኢየሱስን ላለማጥመቅ አንገራገረ። ‹ይመጣል›



ተብሎ የተነገረለት ኢየሱስ እንደሆነ እግዚአብሔር ለመጥምቁ ዮሐንስ አመልክቶት ነበር። (ማቴ. 11፥3) ኢየሱስ ከዮሐንስ የሚልቅ፥ ነገርን ይፈጽማል። ኢየሱስ ሰዎችን የሚያጠምቀው ውኃን በመሰለ ተፈጥሮአዊ ነገር ሳይሆን መለኮታዊ ባሕርይ ባለው በእሳት ነው። ዮሐንስ በዮርዳኖስ ውኃ አጠመቀ፤ ኢየሱስ ግን የሚያጠምቀው በእሳት ፈሳሽ ነው። የኢየሱስ ሰዎችን በእሳት ማጥመቅ በጰንጠቆስጤ ዕለት በተደረገው የሚያከትም ብቻ ሳይሆን፥ ለዘመናት ሁሉ የሚቀጥል ነው፤ ዛሬም እንኳ እያጠመቀ ነው!

አራተኛው ስዕላዊ ገለፃ :- ኢየሱስን የገደሉ ባለ ሥልጣኖችን ከመፍራታቸው የተነሣ 120 ደቀመዛሙርት በአንድ ስፍራ ተሰብስበው ተቀምጠዋል። ኢየሱስ እራሱም :- «ከላይ ኃይልን እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ» (ሉቃ. 24፥49) ብሎ አዝዞአቸው ነበር። ብዙ ጠበቁ፤ ግን ምንም የተደረገ አስደናቂ ነገር አልነበረም።

አሥረኛው ቀን እሑድ ነበር፤ ይህ ዕለት የሳምንታት በዓል ወይም የጰንጠቆስጤ ቀን በመባል ይታወቃል። ከጥዋቱ ሦስት ሰዓት ሲሆን ካህኑ ሕብስቱን በእግዚአብሔር ፊት የሚያቀርብበት ጊዜ ነው። ልክ በዚያው ሰዓት ከኢየሩሳሌም ሰማዮች መለኮታዊ ዐውሎ ንፋስ ወረደ። መንፈስ ቅዱስም ሰማያትን ሰንጥቆ መጣ። ሰማያት ተከፍተዋል፤ እስካሁን ድረስም አልተዘጉም። ጌታ ይመስገን! ኢየሱስ በተሰቀለበት ጊዜ የተቀደደውን የቤተ መቅደስ መጋረጃ ምናልባት ካህናቱ ሰፍተው ሊያያይዙት ሞክረው ይሆናል። በመንፈስ ቅዱስ መውረድ የተዘጋውን ሰማይ ግን አጋንንት ኃይላቸውን በሙሉ አስተባብረው ቢነሱ እንኳ ሊዘጉት አይችሉም። ለዘላለም ክፍት ነው።

ሙሴ እግዚአብሔርን በእሳት ቁጥቋጦ ውስጥ አይቶታል፤ ዛሬ ደግሞ በዚህ ክቡር በር በኩል የመንፈስ ቅዱስ እሳት መጥቶአል፤ ማንም ሊያግደው አይችልም። የእሳት ወላፈን የሚመስሉ ነገሮች ሲጠባበቁ በነበሩት

ደቀ መዛሙርት ራስ ላይ ተቀመጡባቸው። ሰማያዊው ክብር በስፍራው በነበሩት ላይ ወረደ። መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸውና በውጪቸው አደረ። ከዚያ በፊት የሰው ልጅ ይህን በመሰለ ሁኔታ መንፈስ ቅዱስን ተለማምዶ አያውቅም፤ ቃላት ሊገልጹት፥ የሰው አንደበትም ሊናገረው አይችልም። መንፈስ ቅዱስ እንዳነሳሳው ባለቅኔ ሁሉ «የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ» (የሐዋ. 2፥11) እግዚአብሔር ራሱ በሰጣቸው ቋንቋ ይናገሩ ጀመር።

> ሙሴ እግዚአብሔርን በእሳት ቁጥቋጦ ውስጥ አይቶታል። ዛሬ ደግሞ በዚህ ክቡር በር በኩል የመንፈስ ቅዱስ እሳት መጥቶአል፤ ማንም ሊያግደው አይችልም።

## ጥምቀቱና ሌሎች ሥራዎቹ

ደህንነትን ስናገኝ ከመንፈስ ቅዱስ ዳግም እንወለዳለን። ይሁን እንጂ ይህ የሥራው ፍጻሜ አይደለም። ብዙ ሥራዎች አሉት። በተለይም ደግሞ ስለ ክርስቶስ የምንመሰክርበትን ኃይል ይሰጠናል። በጸጋ ድነናል፤ ዳግም ተወልደናል፤ በመንፈስ ኃይል ስለ ክርስቶስ እንድንመሰክር ይህ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ልምምድ ይሰጠናል። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ማለትም ይኸው ነው።

ይህ ምን ያህል አስፈላጊያችን ይመስላችኋል! ደቀ መዛሙርቱ በሽተኛን ፈውሰዋል፤ አጋንንትንም አውጥተዋል። ይህንንም ማድረግ የቻሉት ክርስቶስ አብሮአቸው ስለነበር ነው። ለአገልግሎት ከመውጣታቸው በፊት ከላይ ኃይልን እስኪለብሱ ድረስ እንዲጠብቁ ጌታ ኢየሱስ ራሱ ነግሮአቸው ነበር። የኢየሱስ እናት ማርያም ራስዋ አንድ ምሳሌ ናት። ኢየሱስን የወለደችው በመንፈስ



ቅዱስ ነበር። መንፈስ ቅዱስን በሕይወትዋ ታውቀዋለች። ይሁን እንጂ «አብ የሰጠው ተስፋ» (የሐዋ 1፥4) የተባለለትን የላቀውን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እንድትለማመድ ከሌሎች ደቀመዛሙርት ጋር በኢየሩሳሌም መቆየት ነበረባት። ለእርስዋ አስፈላጊ ከሆነ፥ ለእኛም እጅግ በጣም አስፈላጊያችን ነው። *

በቀላል አገላለጽ ማስቀመጥ ይቻላል። ደቀ መዛሙርቱ የክርስቶስ የቅርብ ተከታዮች መሆናቸውን እርሱ ራሱ መስክሮላቸዋል። እርሱ እዚህ ምድር ላይ እስከነበረበት ጊዜ ድረስ ታላላቅና አስደናቂ ነገሮችን አድርገዋል። እርሱ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ግን ብቸኝነት ተሰማቸው፤ ፍርሃት አደረባቸው። ጌታ ግን :- «ሌላ አፅናኝ» እንደሚልክላቸው ነግሮአቸው ነበር። «ሌላ አፅናኝ» የተባለውም መንፈስ ቅዱስ ነው። (ዮሐ. 14፥16)

«አፅናኝ» የሚለው ቃል በሀዘንም በመከራም የማይለይ ጓደኛ ማለት ነው። ኢየሱስ ለሦስት ዓመታት ያህል አብሮአቸው ነበር፤ የመጀመሪያው ታላቅ አፅናኛቸው እርሱ ነበር። ከዚያ በኋላ ደግሞ «ሌላ አፅናኝ» የተባለው መንፈስ ቅዱስ በጰንጠቆስጤ ቀን ወረደላቸው። መንፈስ ቅዱስን በማግኘታቸው ራሱ ክርስቶስን እንዳገኙ ነበር የተሰማቸው። ስለዚህም ኢየሱስ የሰጣቸውን ወንጌልን የመስበክ አገልግሎት እንደሚገባ ለመወጣት ይችላሉ። እንደ ቀድሞው ሁሉ ሕሙማንን መፈወስ፥ አጋንንትን ማውጣትና ድንቅ ተአምራትን ማድረግ፥ ይችላሉ። ስለ ክርስቶስም በድፍረት መመስከር ይችላሉ። ስለ ክርስቶስ መመስከር ለእያንዳንዱ ዳግም የተወለደ ክርስቲያን የተሰጠ መብትና ኀላፊነት ነው። (ማቴ. 28፥19-20፤ ማር. 16፥15-18)

> በጸጋ ድነናል፤ ዳግም ተወልደናል፤ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስለ ክርስቶስ እንድንመሰክር ይህ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ልምምድ ይሰጠናል። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ማለትም ይኸው ነው።

> በመጀመሪያ፥ ወደ ክርስቶስ መምጣትና ሕይወታችንን ለእርሱ ማስረከብ አለብን፤ ከዚያ በኋላም የመንፈስ ቅዱስን ኃይል መቀበል አለብን። ሕይወታችን ራሱ የትንሣኤው ኃይል ማስረጃ መሆን ይኖርበታል።

እኛም ብንሆን በመጀመሪያ ወደ ክርስቶስ መምጣትና ሕይወታችንን ለእርሱ ማስረከብ አለብን። ከዚያ በኋላም የመንፈስ ቅዱስን ኃይል መቀበል አለብን። ሕይወታችንም ራሱ የትንሣኤው ኃይል ማስረጃ መሆን ይኖርበታል። በቃል መናገሩ ብቻ በቂ አይደለም፤ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በሕይወታቸው የሚገለጽ ክርስቲያኖች ያስፈልጉናል።

«ጥምቀት» የሚለው ቃል ከጥንት ከመሠረቱ ሃይማኖታዊ ትርጉምን የሚያመለክት አልነበረም። ቃሉ አንድን ነገር ወይም ጨርቅን ቀለም ውስጥ ከመንከር ጋር ይመሳሰላል። ልብስ በቀለም ሲነከር የቀለሙን መልክና ባሕርይ ይዞ ነው የሚወጣው ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ሲያጠምቀንም :- «የመንፈሳዊው ባሕርይ ተካፋይ» (2 ጴጥ. 1፥4) እንሆናለን። የእርሱ «መልክ» እና ባሕርይ ይኖረናል። መንፈሱ በውስጣችን፥ እኛም በመንፈሱ ውስጥ እንሆናለን፤ የመንፈስ ቅዱስ ሕዝብ ነን።

ከደቀ መዛሙርቱ ውስጥ አንዳንዶቹ ቢያምኑም ሌሎች ደግሞ ይጠራጠሩ ነበር። (ማቴ. 28፥17፤ ማር. 16፥13፤ እና ሉቃ. 24፥41) ስለዚህም ደቀመዛሙርቱን ታላላቅ ሰዎች ያደረጋቸው ኢየሱስን ማየታቸው ወይም ድምፁን መስማታቸው ነው ማለት አይቻልም። ደቀመዛሙርቱን ታላላቅና ልዩ ሰዎች ያደረጋቸው መንፈስ ቅዱስ ነው። በመጀመሪያ አይሁድን ከመፍራታቸው የተነሣ በራቸውን ዘግተው ተቀምጠው ነበር። (ዮሐ. 20፥19) በጣም ከመፍራታቸው የተነሣ እርስ በርሳቸው እንኳ በድብቅ ነበር የሚገናኙት አንዳንዶቹ ወደ ቀድሞ ሥራቸው ወደ ዓሣ ማጥመድ ተመልሰዋል። (ዮሐ. 21) «ኢየሱስ ሕያው ነው!» በማለት በአደባባዮች ለማወጅ ድፍረት



አጥተዋል። በጰንጠቆስጤ ቀን መንፈስ ቅዱስ ከወረደባቸው በኋላ ግን ይህ ሁሉ ተለውጦአል። አይሁድን ከመፍራት ይልቅ እንዲያውም አይሁድ እነርሱን ፈሩዋቸው። «ወንድሞች ሆይ :- ምን እናድርግ?» በማለት ሐዋርያትን ይጠይቁዋቸው ነበር። ኢየሱስም እንዲህ በማለት ነግሮአቸው ነበር :-

> «ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርቻም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ።» (የሐዋ 1፥8)

## እንዴት እንደ ተጀመረ

እስቲ አሁን ደግሞ አራተኛውን ሥዕላዊ ገለፃ እንመልከት :-

> «በዓለ ኀምሣ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፥ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ፥ ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፤ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው፥ በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።» (የሐዋ. 2፥1-4)

ምን ዓይነት መለኮታዊ ኃይልና ክብር! የሰማዩ አባታችን እግዚአብሔር የማይፈጸም ተስፋ አይሰጥም። ኢየሱስ «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ . . . » (ማር. 16፥15)በማለት አዝዞአቸው ነበር፤ ይህ መለኮታዊ እሳት ስለነካቸው ትእዛዙን ተግባራዊ አደረጉ፤ እግዚአብሔር በመሥራቱ እነርሱም ለሥራ ተነሳሱ። ይህ መጽሐፍ የሐዋርያት ሥራ የተባለበትም ምክንያት ይኸው ነው።

ከሰማይ የሚፈስሰውን ተቀበሉ፤ ከእነርሱ የሚፈልቀው ደግሞ ሌሎችን አጥለቀለቀ። ኢየሱስ «...የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ (ከልቡ) ይፈልቃል ...» (ዮሐ. 7፥38) ብሎ ነበር። ይህ ሰማያዊ ኃይል ለጊዜው ስሜትን የሚያዝናና ብቻ አልነበረም። ደቀመዛሙርቱ «ሰማያዊ ኃይልን እንድናገኝ እስቲ ለሳምንት ያህል እንጸልይ» ማለት አላስፈለጋቸውም። የፈለጉትን አግኝተዋል፤ የፈለጉትን ስላገኙም መለኮታዊ ኃይልን ሲጠይቁ አንመለከትም። ሐዋርያው ጴጥሮስ ለዚያ ሽባ ሰው - «ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ» (የሐዋ. 3፥6) አለው።

ዝም ብለው ተቀምጠው ውሳኔዎችን የሚያጸድቅ ሊቀ መንበር መምረጥ አላስፈለጋቸውም። ለሥራ ተነሳሱ፥ የክርስትና ዘመን ተጀመረ፤ የዓለም ሕዝብም ለመጀመሪያ ጊዜ የምሥራቹን ቃል ሰማ። ታዲያ ምን ውጤት ተገኘ? ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወንጌልን ሲሰብክ የሰሙ ሰዎች ጌታን መቀበል ጀመሩ። በዚያን ቀን ብቻ ሦስት ሺህ ሰዎች ደህንነትን አገኙ። የጰንጠቆስጤ ዓላማውም ይኸው ነው። ደህንነትና ወንጌል የማስፋፋት አገልግሎት የሥላሴዎች እቅድ ነው። አብና ወልድ በኃጢአት የጠፋውን ዓለም ያድን ዘንድ መንፈስ ቅዱስን ላኩት። (ኢሳ. 48፥16)

ዋነኛው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ዓላማም ይኸው ነው። እግዚአብሔር ሰዎችን በማዳን ላይ ነው። እኛስ ምን እያደረግን ነው?

ደህንነትና ወንጌልን የማስፋፋት አገልግሎት የሥላሴዎች ዕቅድ ነው።

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን ያገኘነው ስሜታችንን ለማነቃቃት ሳይሆን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ሆነን የጌታን ሥራ እንድንሠራ ነው። ኢየሱስና መንፈስ ቅዱስ የመጡበትን ዓላማ እናውቃለን። እኛስ እዚህ ያለነው ለምንድነው? በጰንጠቆስጤ ዕለት የፈለቀው ወንዝ ጠቅላላ የሮም ግዛትን አጥለቀለቀ። አንዳንድ ሰዎች «በጥንት ክርስቲያኖች ዘመን ኖረን ቢሆን ኖሮ» ይላሉ። ሁኔታውን



ልዩ ያደረገው ግን ዘመኑ ወይም በዘመኑ የነበሩት ሰዎች አልነበሩም። ሁኔታውን ልዩ ያደረገው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው። የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ባይኖራቸው ኖሮ፥ ምናልባት ዓሣ ወደ ማጥመድ ሥራቸው በተመለሱ ነበር። ከኢየሱስ ጋር በነበሩበት በወጣትነታቸው ዘመን ያዩትን አስደናቂ ነገሮች እየተረኩ አርጅተው እንደማንኛውም ሰው በሞቱ ነበር። እነርሱ ግን ዓለምን ለወጧት። ያ ጥምቀት ለሁላችንም ነው።

> ደህንነትና
> ወንጌልን
> የማስፋፋት
> አገልግሎት
> የሥላሴዎች
> እቅድ ነው።

## ለዘመናችንም

አንዳንድ ሰዎች የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና የሌሎችም ድንቅና ተአምራቶች አስፈላጊነት ለጥንት ክርስቲያኖች ብቻ ነበር። አስፈላጊነቱም «ቤተ ክርስቲያን እስክታድግ» ድረስ ብቻ ነበር፤ ዛሬ ግን አያስፈልጉም በማለት ያስተምራሉ። ያለመንፈስ ቅዱስ ተአምራዊ ስጦታዎች ክርስቲያኖች መኖር ይችላሉ ይሉናል። ይህ አባባል ደግሞ የጥንት ክርስቲያኖችን በመጀመሪያ ደረጃ፥ እኛን ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ ያደርገናል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን እንደዚህ አያስተምርም። ይህ አባባል ያለማመን ውጤት ነው። ቤተክርስቲያን ከተመሠረተች ሃያ ዓመት በኋላ ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ኤፌሶን በሄደበት ወቅት እንኳ አስራ ሁለት ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀዋል። (የሐዋ. 19፥6-7) ማንኛውም ትውልድ ቢሆን የጰንጠቆስጤ ኃይል ያስፈልገዋል። በ30 ዓ.ም የዓለም ሕዝብ ብዛት አንድ መቶ ሚሊዮን ነበር። ዛሬ ግን ስድስት ቢሊዮን ሆኖአል፤ በከፍተኛ ፍጥነትም እያደገ ነው። ከመጀመሪያው ክፍለ - ዘመን ከነበሩት ይልቅ ዛሬ በአሥር እጅ የሚበልጡ ሰዎች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት አያውቁም። አለማመንና

ለእግዚአብሔር ደንታ-ቢስነት ከማንኛውም ጊዜ በዘመናችን ተስፋፍቶአል። ያለ አንዳች ጥርጥር የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለዚህ ዘመን አስፈላጊያችን ነው።

ስለዚህም ሐዋርያቱ የተለማመዱት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለዘመናችን ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን ከመጽሐፍ ቅዱስ ላሳያችሁ እፈልጋለሁ። እስቲ እናንተው ራሳችሁ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ጴጥሮስ በጰንጠቆስጤ ዕለት ተሰብስበው ለነበሩት ሰዎች የሰበከውን ስብከት አንብቡት። የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት መቀበል ያለባቸው እነማን እንደሆኑ ሲያመለክት እንዲህ አለ ፦

> «የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና።» (የሐዋ. 2፥39)

በመጀመሪያ ደረጃ ፦ «ለእናንተ» አላቸው «ኢየሱስንም በዓመፀኞች እጅ ሰቅላችሁ ገደላችሁት»። (የሐዋ. 2፥23) በማለት የወቀሳቸውም እነዚህኑ ሰዎች ነበር። አሁን ግን ፦ «ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ» (የሐዋ. 2፥38) ይላቸዋል። ኢየሱስም ፦ «ክፉ ትውልድ» (ሉቃ. 11፥29) «የማያምን ጠማማ ትውልድ» (ማቴ. 17፥17፤ ሉቃ.9፥41) በማለት የገሰጸውም ይህንኑ ሕዝብ ነበር።

በሁለተኛ ደረጃ ፦ «ልጆቻችሁ» አላቸው። ልጆቻችሁ ሲል ሁለተኛ ትውልድን ያመለክታል። አንዳንድ ሰዎች በስተርጅናቸው ነው የሚወልዱት። የጰንጤቆስጤ ቀን ካለፈ 100 ዓመት ቢያልፈውም ሰዎች ይህን በረከት ተቀብለው በልሳን መናገር ይችሉ ነበር። «ልጆች» ሲል ከአንድ ቤተሰብ የሚወለዱ ልጆችን ሳይሆን ትውልድን ማመልከቱ ነው።

በሦስተኛ ደረጃ ፦ «ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ» (ማቴ. 28፥19-20፤ ማር.16፥15-16 አለ። «ለሚጠራቸው» የሚለው ወደ



ክርስቶስ የሚመጡትን ሰዎች ያመለክታል። ኢየሱስ «የላከኝ አብ (እግዚአብሔር) ካልሳበው በቀር ማንም ወደ እኔ አይመጣም» (ዮሐ. 6፥44 ) ብሎአል። ጴጥሮስና አብረውት የነበሩ 119 ሰዎች፤ እንደተቀበሉ ሁሉ ማንኛውም አማኝ መንፈስ ቅዱስን መቀበል ይችላል። ደቀመዛሙርቱ እንዳደረጉት አድርጉ፤ እነርሱ ያገኙትንም ታገኛላችሁ። ለሁላችንም የተሰጠንን ተስፋ እመኑ - «መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ»። (ኤፌ. 5፥18)

በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ ማንም ሳይሆን ኢየሱስ ብቻ ነው። የግልህ የጴንጠቆስጤ ልምምድ ይኑርህ እንጂ፥ በሌሎች ልምምድ አትታመን። የሌሎች ልምምድ የአንተ ሊሆን አይችልም። መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዱ ሐዋርያ ላይ ተቀመጠ (የሐዋ. 2፥3) እንጂለተወሰኑት ብቻ አልነበረም የወረደው። መንፈስ ቅዱስ በግልህ ይሰጥሃል።

> በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ ማንም ሳይሆን ኢየሱስ ብቻ ነው፤ የግልህ የጰንጠቆስጤ ልምምድ ይኑርህ እንጂ በሌሎች ልምምድ አትታመን። የሌሎች ልምምድ የአንተ ሊሆን አይችልም።

መንፈሳዊ ቅዝቃዜና ጨለማ በዋጠው ዓለም ነው ያለነው ቅዝቃዜው ወደ በረዶነት እንዳይለውጠን የመንፈስ ቅዱስ እሳት ያሙቀን። እግዚአብሔር በልቦናህ መሰዊያ ላይ እሳቱን ያነድዳል። ሌሎችን አሙቅ እንጂ ሌሎች እስኪያሞቁህ አትጠብቅ።

**ክፍል ሁለት**

# የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት እንዴት ማግኘት እንደሚቻል።

## ሰጪውን ማመን።

በየስፍራው በምናደርገው ታላላቅ የወንጌል ስብሰባ በሺህ የሚቆጠሩ የማያምኑ ሰዎች ይመጣሉ። አንዳንዶቹ የታወቁ ወንጀለኞች ምግባረ-ብልሹዎች፥ ለተለያዩ ሱስ ተገዥዎች፥ በሟርት በጥንቆላ የተተበተቡ ናቸው። ሃይማኖተኞች ቢሆኑም ሃይማኖታቸው ሊረዳቸው አልቻለም። እነዚህ ሰዎች በመጀመሪያ ደህንነትን ማግኘት አለባቸው። ሐዋርያው ጳውሎስ በዘመኑ ለነበሩት አማኞች - «ከእናንተም አንዳንዶቹ እንደ እነዚህ ነበራችሁ፤ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል ተቀድሳችኋል፥ ጸድቃችኋል» (1 ቆሮ. 6፥11) ይላቸዋል። ወደ ስብሰባችን የሚመጡት ሰዎች ከዚያ አስቀድሞ እርኩሳን መናፍስት ያደሩባቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ይሁን እንጂ በመቶ ወይም በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ቤተ መቅደስ ሲሆኑ በየጊዜው እንመለከታለን።

ሁለት መንገዶች ብቻ ናቸው ያሉት- በመጀመሪያ ኅጢአትን መናዘዝ፤ በሁለተኛ ደረጃ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን።



እንዴት? ሁለት መንገዶች ብቻ ናቸው ያሉት በመጀመሪያ ኃጢአትን መናዘዝ፤ በሁለተኛ ደረጃ፥ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን።

## ኃጢአትን መናዘዝ (ንስሐ)

ኢየሱስ እንዲህ አለ - «እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤ ... ዓለም ሊቀበለው የማይችለው የእውነት መንፈስ ነው።» (ዮሐ. 14፥16-17) ሐዋርያው ጴጥሮስ ደግሞ እንዲህ ብሏል - «እንግዲህ ከጌታ ፊት የመጽናናት ዘመን እንድትመጣላችሁ አስቀድሞም ለእናንተ የመረጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲልክላችሁ ኃጢአታችሁም ይደመሰስ ዘንድ ንስሐ ግቡ ተመለሱም ... የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።» (የሐዋ. 3፥19፤ 2፥38)

ከኃጢአት የምንነጻበት ሌላ መንገድ የለም። ቅዱስ ወይም ንጹሕ የሚያደርገን የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ብቻ ነው መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ስጦታ እንጂ፥ በጥረታችን ወይም በብቃታችን የሚገኝ አይደለም።

ከኃጢአት የምንነጻበት ሌላ መንገድ የለም። ቅዱስ ወይም ንጽህ የሚያደርገን የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ብቻ ነው መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ስጦታ እንጂ፥ በጥረታችን ወይም በብቃታችን የሚገኝ አይደለም።

መንፈስ ቅዱስ እጅግ በጣም ንጹሕ ባሕርይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስን በእርግብ ይመስለዋል። እርግብ በጣም ንጹሕ ወፍ በመሆንዋ ጐጆዋን ቆሻሻ ስፍራ ላይ አታደርግም። መንፈስ ቅዱስም እንዲሁ በጣም ቅዱስ

በመሆኑ በኃጢአት በተበከለ አካል አያድርም። ይህ ስማያዊ ውኃ ቆሻሻ በደፈነው አሸንዳ፥ በረከሰ አእምሮ ወይም ባልተቀደሰ አንደበት አያልፍም።

መንፈስ ቅዱስ የሚሰጣቸው በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ታጥበው የእግዚአብሔር ልጆች ለሆኑት ብቻ ነው። በጐልጐታ በፈለቀው ምንጭ ካልታጠበ በቀር ማንም ንጹሕ ሊሆን አይችልም። ከእሳቱ ደሙ ይቀድማል። ከኃጢአት የምንነጻበት ሌላ መንገድ የለም። ቅዱስ ወይም ንጹሕ የሚያደርገን የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ብቻ ነው። መንፈስ ቅዱስም የእግዚአብሔር ስጦታ እንጂ፥ በጥረታችን ወይም በብቃታችን የሚገኝ አይደለም።

## በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ማመን (እምነት)

«ያለ እምነትም እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና»። (ዕብ. 11፥6)

«ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ቅዱስ ተናገረ።» (ዮሐ. 7፥39)

> ማንም ወደ ኢየሱስ ለመምጣት መለመን ወይም መወትወት የለበትም። ይህ እምነት አይደለም፤ እምነት መቀበል ማለት ነው።

«የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች ሆይ፥ ... በሕግ ሥራ ወይም ከእምነት ጋር በሆነ መስማት መንፈስን ተቀበላችሁን?» (ገላ. 3፥1-2)

ማንም ቢሆን ወደ ኢየሱስ ለመምጣት መለመን ወይም መወትወት የለበትም። ይህ እምነት አይደለም። እምነት መቀበል ማለት ነው። በተቀደሰው እሳቱ



እንዲያጠምቅህ ኢየሱስን መለማመጥ የለብህም። እንደሚሰጥህ እርሱ ራሱ ቃል ገብቶአል። የሚሰጥህን ለመቀበል በሙሉ ልብህ ቅረበው፤ ስጦታውን ከመቀበልህ በፊት በስጦታው ባለቤት እመን።

ታዲያ፥ ኢየሱስ ራሱ ደቀመዛሙርቱን «በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ» ለምን አላቸው? ምክንያቱም በዚያ ጊዜ - «ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና» (ዮሐ. 7፥39) ነው። ያ ታሪካዊ ሁኔታ እስኪፈጸም ድረስ መቆየት ነበረባቸው። አሁን ግን እዚሁ ነው ያለው። የጴንጠቆስጤ ልምምድ በእውነት ላይ የተመሠረተ ነው። አንተ ራስህ በሕይወትህ ልታረጋግጠው ትችላለህ። የመቀበል እንጂ፥ የልመና ስብሰባዎችን አናካሂድም። ኢየሱስ ቃሉን በሕይወታችን ለመፈጸም ፈቃደኛ ነው። አማኞች እንጂ ለማኞች አይደለንም።

## ቅዱስ ቋንቋ

በመጀመሪያ በመንፈስ ቅዱስ ስንጠመቅ የሚከተለው ሁኔታ በሕይወታችን ይፈጸማል -

«በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።» (የሐዋ. 2፥4)

እንዴት? መቶ ሃያዎቹ ደቀመዛሙርት ጌታን እያመሰገኑ ነበር። ወዲያው «ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ» (የሐዋ. 2፥2) «የተከፋፈሉ የእሳት ልሳኖች» ተመስሎ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው። ልባቸው በደስታ ተሞላ። ለመናገር አፋቸውን ሲከፍቱም መንፈስ ቅዱስ ከዚያ በፊት የማያውቁትን ቋንቋ ሰጣቸው። እኛ የምንቀበለውም እነርሱ የተቀበሉትን መንፈስ ከሆነ፥ ውጤቱም ልክ እንደ እነርሱ መሆን አለበት። በመንፈስ የሚያጠምቀው ኢየሱስ አልተለወጠም፤ የአሠራር

> እኛ የምንቀበለውም እነርሱ የተቀበሉትን መንፈስ ከሆነ ውጤቱም ልክ እንደ እነርሱ መሆን አለበት በመንፈስ የሚያጠምቀው ኢየሱስ አልተለወጠም፤ የአሠራር መንገዱም አልተለወጠም። በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የቅጂዎች ቅጂ አይደለንም። የመጀመሪያውን ልምድ የመጀመሪያ ከሆነው ጌታ እንቀበላለን፤ የመጀመሪያውም ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ነው።

መንገዱም አልተለወጠም። በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የቅጂዎች ቅጂ አይደለንም፤ የመጀመሪያውን ልምምድ የመጀመሪያ ከሆነው ጌታ እንቀበላለን። የመጀመሪያውም ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ነው።

«ከጴጥሮስ ጋር የመጡት ሁሉ ከተገረዙት ወገን የሆኑ ምዕመናን በአሕዛብ ላይ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ስለፈሰሰ ተገረሙ፤ በልሳናት ሲናገሩ፥ እግዚአብሔርንም ሲያከብሩ ሰምተዋቸዋልና።» (የሐዋ. 10፥45-46)

በልሳን መናገር የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ማስረጃ እንደሆነ ነበር ሐዋርያው ጳውሎስ የተረዳው። አስማተኛው ሲሞንም ይህን «አየ»። ያየውም መንፈስ ቅዱስ በመለኮታዊ ሁኔታ ራሱን ሲገልጽ ለመሆኑ ጥርጥር የለንም። (የሐዋ. 8፥17-19) ጳውሎስ ራሱ በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቋል። (የሐዋ. 9፥17) በልሳን ይናገር እንደነበረም ገልጾአል። (1 ቆሮ. 14፥18) በሌላ ስፍራም ተመሳሳይ ሁኔታ መታየቱ ተገልጾአል። (የሐዋ. 11፥17፤ 13፥52፤ 19፥6)

በጰንጠቆስጤ ዕለት ስለተፈጸመው ሁኔታ ጴጥሮስ ከነቢዩ ኢዮኤል በመጥቀስ ማብራሪያ ሰጠ። (የሐዋ. 2፥17-19) ሰዎች ትንቢት እንደሚናገሩ ኢዮኤል አመልክቶ ነበር። ሰዎች በልሳን ሲናገሩ ሁኔታው የኢዮኤል ትንቢት ፍጻሜ እንደሆነ «በነቢዩ ኢዮኤል የተባለው ይህ ነው»። (የሐዋ. 2፥16)



በማለት አመለከተ። በልሳን መናገር ሲተረጐም ትንቢት ይሆናል።

> ልሳን ሰይጣን ሊያስተውለው የማይችለው ብቸኛ ቋንቋ ነው። የመንፈስ ቅዱስን ቋንቋ እንዷንም ፊደል እንኳ መረዳት ስለማይሆንለት ግራ የሚያጋባን ሰይጣን ራሱ ግራ ይጋባል፥ከሰማያዊ ዙፋን የሚያገናኘንን የመንፈስ ቅዱስ የሚስጥር ቋንቋ (ኰድ) መጥለፍ አይቻለውም።

ለወንጌል አገልግሎት ስንሰማራ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን መሆኑን እንድንታመን እግዚአብሔር ከዚህ የተሻለ ምን ምልክት ሊሰጠን ይችላል? እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ሁሉ አንዳንዴ በፍርሃትና በድካም (1 ቆሮ. 2፥3) ልንሆን እንችላለን፤ መንፈስ ቅዱስ ግን ዋስትናችን ነው። ያለምንም ዋስትና መጸለይ ይቻላል። ዛሬ ሲፈጸም የምናስተውለውም ይህንኑ ነው።

አስደናቂ ስጦታ! በልሳን መጸለይ ለእግዚአብሔር ሚስጥርን መናገር እንደሆነ ጳውሎስ ያመለክታል። (1 ቆሮ. 14፥2) ልሳን ሰይጣን ሊያስተውለው የማይችለው ብቸኛ ቋንቋ ነው። የመንፈስ ቅዱስን ቋንቋ አንዷን ፊደል እንኳ መረዳት ስለማይሆንለት፥ ግራ የሚያጋባን ሰይጣን ከሰማያዊ ዙፋን ጋር የሚያገናኘንን የመንፈስ ቅዱስ የሚስጥር ቋንቋ (ኰድ) ሊጠልፍ አይቻለውም።

ስለ መንፈስ ቅዱስ ስንጸልይ መንፈስ ቅዱስ ራሱ ግን ጠቅላላ ሁለንተናችንን ማለትም መንፈሳችንን ነፍሳችንን አዕምሮና አካላችንን ይዳስሳል።

ሰውነታችን የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ነው። (1 ቆሮ. 6፥19) ኢየሱስም ቤተ መቅደስ የጸሎት ቤት እንደሆነ አመልክቶአል። (ማቴ. 21፥13፤ ማር. 11፥7) እንግዲህ ሰውነታችን መቅደስ ወይም መንፈስ ቅዱስ የሚያድርበት የጸሎት ቤት ከሆነ፥ እርሱ ራሱ በውስጣችን ሆኖ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን የሚደርስ ንጹሕና ኃይለኛ ጸሎትን ይጸልያል ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ መጸለይን

> ስለ መንፈስ ቅዱስ ስንጸልይ መንፈስ ቅዱስ ራሱ ግን ጠቅላላ ሁለንተናችንን ማለትም ፡- መንፈሳችንን ነፍሳችንን፥ አእምሮና አካላችንን ይዳስሳል።

ይወድዳል፤ በመንፈስ የተሞሉትም መጸለይ የሚወዱት ከዚህ የተነሣ ነው። ይህ ደግሞ አሰልቺና አድካሚ ግዴታ ሳይሆን አስደሳችና ጣፋጭ መብት ነው። ኢየሱስ - «የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ... እርሱ ያከብረኛል» (ዮሐ. 16፥13-14) አለ።

ሰለሞን ቤተ መቅደሱን በመረቀበት ጊዜ የእግዚአብሔር ክብር ብርሃን ቅድስተ ቅዱሳኑን ሞላው። ከዚህም የተነሣ ካህናቱ ወደ ቤተ መቅደሱ መግባት ወይም ለማገልገል አልቻሉም። በግንባራቸው ተደፍተው እግዚአብሔርን አመለኩ፤ ክብርና ውዳሴም አቀረቡለት። (2 ዜና. 7፥1-3) ይህ የብሉይ ኪዳን ምሳሌ ነው።

ደህንነትን ያገኘን ከሆነ፤ የክርስቶስ ብርሃን በልባችን መቅደስ ያድራል፤ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስንጸልይ ግን መንፈስ ቅዱስ እርሱ ጠቅላላ ሁለንተናችንን ማለትም መንፈሳችንን፥ ነፍሳችንን፥ አእምሮና አካላችንን ይዳስሳል። መላውን ሰብዕናችንን ያጕርፋል።

## ሰይጣን ድርሻ የለውም

በመጨረሻም ማድረግ የሚገባህ ነገር ቢኖር መጠየቅ ብቻ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የነጻን ከሆንን የእግዚአብሔር ልጆች ነን። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ደግሞ የልጅነት መብታችን ነው። ኢየሱስም ይህን ስጦታ ጠይቀን እንድናገኝ ሲያደፋፍረን - «ጠይቁ ... ፈልጉ ... አንኳኩ ... የሚጠይቅ ሁሉ ይቀበላል፤ የሚፈልግም ያገኛል፤ መዝጊያንም ለሚያንኳኳ



ይከፈትለታል። (ሉቃ. 11፥9-10) ብሎናል። ስለዚህ ያለአንዳች መጠራጠር በእምነት ጠይቀው። (ያዕ. 1፥6)

> ማንኛውም ቆሻሻ ርኩስ መንፈስ ማንነቱን በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ ሰውሮ መምጣት አይቻለውም።

ከእግዚአብሔር የምንቀበለው ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው የሚሆነው። ሰይጣን በኢየሱስ ስም ለጸለይነው ጸሎት መልስ ሊሰጠን አይችልም። የሰማዩ አባታችንን መንፈስ ቅዱስን እንዲሰጠን ስንጠይቀው ሰይጣን ወደ ሰማይ ለማቅናት ሊረዳን አይችልም።

ማንኛውም እርኩስና ቆሻሻ መንፈስ፥ በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ ማንነቱን ሰውሮ መምጣት አይቻለውም። እስቲ ኢየሱስ ራሱ የተናገረውን እናንብብ ፡-

> «አባት ከሆናችሁት ከእናንተ ማንኛችሁም ልጁ እንጀራ ቢለምነው፥ እርሱም ድንጋይ ይሰጠዋልን? ዓሣ ደግሞ ቢለምነው በዓሣ ፋንታ እባብ ይሰጠዋልን? ወይስ እንቁላል ቢለምነው ጊንጥ ይሰጠዋልን? እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?» (ሉቃ. 11፥11-13)

ይህ ነው እንግዲህ የመጨረሻው መልስ። ከዚህ የተሻለ ደግሞ ምንም ዋስትና ወይም ማረጋገጫ ሊኖረን አይችልም።

## አሁኑኑ ማድረግ የሚገባህ

ይህን አነስተኛ መጽሐፍ አንብበሃል። ጌታ በመንፈስ ቅዱስ ሊያጠምቅህ ፈቃደኛ መሆኑን ተረድተሃል።

> ኃጢአትህ የእግዚአብሔር በግ በሆነው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ታጥቦልህ ከሆነ ይህን ታላቅና ክቡር ስጦታ ለመቀበል ብቁ ነህ ማለት ነው።

በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ ኢየሱስ ብቻ መሆኑን አትዘንጋ። (ዮሐ. 1፥33) በአሁኑ ሰዓት እንኳ አብሮህ ነው ያለው። ኃጢአትህ ሁሉ የእግዚአብሔር በግ በሆነው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደም ታጥቦልህ ከሆነ፥ ይህን ታላቅና ክቡር ስጦታ ለመቀበል ብቁ ነህ ማለት ነው። ሌላ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እስኪደረግ እንኳ መጠበቅ የለብህም። በአሁኑ ቅጽበት እንኳ ኢየሱስ አብሮህ ነው ያለው። ስሙን ማመስገን ጀምር አሁኑኑ ጠይቀው። ጌታን አምልከው። ኢየሱስ ክርስቶስም በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቅሃል።

ኢየሱስ ይወድሃል፤ ከዚህም የተነሣ አንተም ሆንህ ማንም የጥንት ክርስቲያኖች ያገኙትን ሁሉ ማግኘት ትችላላችሁ። ኢየሱስ ይህን እንዲያደርግልህ እንድትወተውተው አይፈልግም። የወደደህ ስለወተወትከው እንዳልሆነ አስተውል። ስለሚወድህም አሁኑኑ በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቅሃል።